**ሳምንታዊ ዜና (ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የጎንደር ሕዝብ በመለስ ንግግር ተበሳጭቶ ተቃውሞ አሰማ፣ የመተማ ወረዳ ለሱዳን መካለሉ ተጋለጠ፣ የአርማጭሆ ሕዝብ አሻፈረኝ ብሎድንበር አይካለልም በማለት ከወያኔ ካድሬዎች ጋር ተፋጧል፣ ጉዳዩ ላይ ጦሩ አሁንም እያጉረመረመ ነው፣ በወለጋ ከ130 በላይ ዜጎች ያለቁበትን ጭፍጨፋ የፈፀመው ወያኔ መሆኑን ህዝቡ አጋለጠ፣ 10 የወያኔ የፌዴራል ፖሊሶች ተገደሉ በርካቶች ቆስለው ጦር ሀይሎች እና ፖሊስ ሆስፒታል ገቡ፣ በቅርቡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባለስልጣናት ላይ ከተቃዋሚ ታጣቂ ሀይሎች ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል ምንጠራ ሊጀመር ነው፣ በአዲስ አበባ በነባር ካድሬዎችና በአዲሶቹ መካከል ሽኩቻ ተጀመረ »»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ …………………………….**

የጐንደር ሕዝብ በተለይ የአርማጭሆና የመተማ አካባቢ ነዋሪዎች በወያኔ ድርጊት እየተበሳጩ ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የአርማጭሆ አካባቢ ነዋሪዎች በወያኔ ድርጊት እየተበሳጩ ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ ላይ የእኛን መሬት ሳይሆን የነሱን መሬት ነው መልሰን የሰጠናቸው፣ በዚህ የተነሳ አንድም የታሰረና የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ የለም በማለት በሰጠው መግለጫ ምክንያት የጐንደር ሕዝብ ክፉኛ በመቆጣቱ የተነሳ በየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ ሳይቀር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊት በአካባቢው መስፈሩ ታውቋል::

ታሪክንና ሀገረን ማፍረስ ስራው የሆነው ወያኔ ከኢትዮጵያ መሬት ቆርሶ ለሱዳን ከሰጠ በኋላ የሀገሪቱ ዜጐች ታፍሰው በጠራራ ፀሐይ እየተጋዙ ባለበት ወቅት ያለ አንዳች ሀፍረትና ይሉኝታ የታሰረ የለም ይበል እንጂ በሱዳን ካምፕ ውስጥ ከታሰሩት መካከል በምግብ አለመስማማት የተነሳ ለከፍተኛ ስቃይ እየተዳረጉ መሆኑንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

የወያኔ ቡድን ለሀገሩና ለሕዝቡ ምንም ደንታ የሌለው በመሆኑ እንጂ ይህ ችግር ዛሬ የተከሰተ ሳይሆን የቆየ ነው:: በተለይም በ1998 ዓ.ም. ታህሳስ ወር ላይ የሱዳን ወታደሮችና ሚሊሻዎች የኛን ድንበር ጥሰው በመግባት በአካባቢው በእርሻ ልማት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን እና በስራ ላይ ተቀጥረው የነበሩ እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪ አርሶ አደሮችን ገድለውና አቁስለው ከመሄዳቸውም በተጨማሪ ለውቂያ የደረሰ ማሽላ አቃጥለው እንደነበር ያስታወሱት የአካባቢው ነዋሪዎች በወቅቱ አንዳችም እርምጃ በወያኔ በኩል ባለመወሰዱ ሲቆጭና ሲቃጠል የነበረው የጐንደር ሕዝብ እትብቱ የተቀበረበትን መሬት ነጥቆ መውሰዱ ሕዝቡን ከመግደል የማይተናነስ ነው ሲሉም በቁጭትና በእልህ ይገልፃሉ::

በመሠረቱ የደርግ ሥርዓት ሲወድቅ የወያኔ በድን ሲተካ በዚህ መካከል ግርግር ስለነበር የሱዳን ወታደሮች በ1983 መጨረሻና በ1984 ዓ.ም መተማ ዋንግ የተባለውን ወንዝ ይዞ በአርማጭሆ በመዞር ተከዜ ድረስ ገብተው የነበረ ቢሆንም ሕዝቡ በመቆጣቱ የተነሳ በወቅቱ ሲያርሱ የነበረውንና የዘሩትን አዝመራ እንኳዋን ሳይሰበስቡ የሸሹ መሆኑን ያስታወሱት የአካባቢው ነዋሪዎች ዛሬ በግላጭ የወያኔው መሪና ጄሌዎቹ ገና ለገና በአካባቢው ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይል ይንቀሳቀስበታል በሚል

ፍርሀትና ከራስ ወዳድነት የመነጨ ስሜት ተነስቶ እንዲህ ያለ አሳፋሪና ወራዳ በሆነ ሁኔታ የሀገርን መሬት ቆርሶ መስጠቱ ሳያንሰው የነሱ ነው ብሎ መከራከሩ እጅግ እንዳሳዘናቸውና ክፉኛ እንደተበሳጩ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

በተለይም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በሰጠው መግለጫ ምክንያት ያዘነው የጐንደር ሕዝብ በንዴትና በእልህ በእንባ ሲራጭ ነበር ያለው ይኸው ከአካባቢው የደረሰን ዘገባ ቀድሞም በወያኔ ቡድን ላይ ቅንጣት ታክል እምነት ያልነበረው ቢሆንም አሁን ደግሞ በመለስና በጀሌዎቹ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያሳደረ ከመሆኑም በላይ በርካታ የብአዴን ካድሬዎች ሳይቀር ድርጊቱን እያወገዙ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ አስረድቱዋል።

በአርማጭሆና በመተማ ወረዳ ውስጥ ያሉ የብአዴን ካድሬዎች መለስ ዜናዊ መግለጫ ከሰጠ በኋላ እርስ በእርስ ክፍፍል ተፈጥሮ ከፍተኛ ግጭት እንደተከሰተ የደረሰን ዘገባ ገልፆ ድርጊቱን እንዲቆጣጠር ወደ ስፍራው የተጓዘው ሠራዊት ጣልቃ ገብቶ ሁኔታውን ለማረጋጋት የቻለ ቢሆንም ጥያቄው በጦሩም ውስጥ ዘልቆ በመግባቱ የተነሳ በቅርቡም የምንጠራ ዘመቻ ሊደረግ እንደሚችል ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቱዋል።

ከስፍራው የመጡ አንድ የመተማ አካባቢ ተወላጅ እንዳሉት የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው ታሪክ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ድንበር ማካለሉ አልተጀመረም እያለ የሚያቅራራው እጅግ ከእውነት የራቀ ሐሰት ነው ካሉ በኋላ በተለይ በመተማ በኩል ድንበር ማካለሉ ተጠናቋል። በአርማጭሆ በኩል ግን ሕዝቡ ገንፍሎ በመውጣቱ ለጊዜው ሕዝቡ እስኪረጋጋ ድረስ ይቋረጥ ተብሎ ሳይካለል ቀረ እንጂ ሁሉም አልቋል ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ገልፀዋል።

አክለውም የሚገርመው በ1998 ዓ.ም በመተማ ብቻ 474 የእርሻ ባለሀብቶችን ጨምሮ ገበሬዎች የተፈናቀሉ እንደነበር አስታውሰው መለስ በሰጠው የውሸት ድራቶ ሕዝቡ እንዳይታለል ጥሪ አቅርበዋል።

ለደህንነቴ ስሜ አይገለፅ ያሉት እኚሁ ከአካባቢው ወደ አዲስ አበባ የመጡ የመተማ ተወላጅ እንዳሉት ከሆነ ወያኔዎች ለራሳቸው መጠቀሚያ በሆነው ቴሌቭዥን ውስጥ መለሰ ጌጡ የተባሉ ባለ ሀብት በጎንደር ያለው ሁኔታ እንዳስደሰታቸው ገለፁ ተብሎ መነገሩ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው ሰውየው ብዙ የእርሻ ልማት መሬት ተወስዶበት በአካባቢው ካድሬዎች እልባት በማጣቱ አዲስ አበባ መጥቶ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር የሆነውን የወያኔው ጀሌ አዲሱ ለገሰን ለማነጋገር ነበር። ነገር ግን ያ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆኑ እየታወቀ የመተማን እና የአርማጭሆን ህዝብ ብሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማታለል እንዲህ ያለ አይን ያወጣ ውሸት መነገሩ እጅግ ያሳፍራል ሲሉም በቁጭት ይገልፃሉ።

በአሁን ሰዓት ስላለው የአካባቢው ሕዝብ ስሜት ሲገልፁም የአካባቢው ሕዝብ አድብቷል። በተለይ መለስ ከተናገረ ቀን በኋላ እጅግ ክፉኛ አዝኗል። የሚሆነውን አሁን መግለፅ ያዳግተኛል። ወደፊት አብረን የምናየው ይሆናል ሲሉም አብራርተዋል።

በአካባቢው የሰፈረው ጦር መካከልም ልዩነቱ እየሰፋ ከመሆኑም በላይ በቅርቡ ግምግማ ይደረጋል በሚል በጦሩ ውስጥ እየተናፈሰ እንደሚገኝም ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል።

በመተማ በኩል የድንበር ማካለሉ ሂደት በመጠናቀቁ የሱዳን ጦር በአካባቢው በየቀኑ ቁጥሩ እየጨመረ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልጾ ወያኔም ቁጥሩ ቀላል የማይባል ወታደሮችን ወደዚያው እያጉዋጉዋዘ መሆኑን ዘገባው አስረድቱዋል።

የሱዳን መንግስት ሰፊ የእርሻ ቦታ ከመውሰዱም በተጨማሪ ከዶሎላ እስከ ነፍስ ገበያ ድረስ600 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለውን ቦታ በወታደሮቹ ተቆጣጥሮ የአካባቢውን ሕዝብ የቁም ስቅሉን እያሳየው ይገኛል ሲሉ አንድ የፓርላማ ተመራጭ ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰዓት ከ1200 በላይ አባወራ ገበሬዎች ተፈናቅለው ያለ ምግብና መጠለያ ቀርተዋል ያሉት እኚሁ የሱዳን ወታደሮች 80 ገበሬዎችን አፍሰው የት እንዳደረሱዋቸው አይታወቅም ካሉ በሁዋላ በሚያሳዝን ሁኔታም አንድ ገበሬን እጅና እግሩን የፊጥኝ አስረውት በእሳት አቃጥለውታል ብለዋል።

ከዚህ ሌላም 6ገበሬዎችን በጥይት የገደሉዋቸው ሲሆን እነሱም ሁነኛው ሙላት፤ፀሐይነህ መሰለ፤አያልነህ ወርቁ፤ሃይሉ ለጋስ፤ደምሳሽ ቦጋለ፤እንደሚባሉ አብራርተዋል።ይህ ሁሉ ግፍና መከራ በዝጎች ላይ ሲፈጸም አንዲትም እንቅስቃሴ ያላደረጉት ወያኔዎች በቅርቡ አዲሱ ለገሰና ሳሞራ የኑስ ወደ አርማጭሆና መተማ ሄደው ህዝቡን ለመስበክ የሞከሩ ቢሆንም ሳይሳካላቸው መቅረቱን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

በተመሳሳይ ጐንደር በኩል ከፍተኛ ወንጀል የፈፀመው ወያኔ በምስራቅ ውለጋ በኩልም አሰቃቂ እልቂት እንደፈፀመ ከስፍራው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።
ግንቦት 9 ቀን ከጧቱ 3 ሰዓት እስከ 10 ሰዓት ድረስ መትረየስ፣ ላውንቸር ቦምብና ክላሽ በታጠቁ ኃይሎች በሳሲጋ ወረዳ ውስጥ በተፈጠረው ጭፍጨፋ ከ130 በላይ ሰዎች ለሞትና በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ለመቁሰል አደጋ የተዳረጉ ሲሆን ከ10 ሺህ በላይ ደግሞ ለስደት መዳረጋቸው ታውቋል።

ወያኔ በአሁን ሰዓት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ የደረሰበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተወሰነ ጊዜ ማግኛ እያለ በሚፈጥራቸው ሰንካላ ድርጊቶች ወለጋ ውስጥ የተከሰተውን እልቂት የፈፀመው እራሱ ነው ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች መግለፃቸውን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

የወታደራዊ ልብስ የለበሱ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁ ኃይሎች ጥቃቱን የሰነዘሩ መሆኑን የገለፁት የአካባቢው ነዋሪ የነበሩት ሰዎች በመትረየስ በታገዘ በቀላል የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ሕዝቡን በየእርሻ መሬት በመሄድና በየቤቱ በመግባት ያለምንም ጥያቄ ጭፍጨፋውን ያካሄዱ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ፊታቸው እንዳይታይ በጨርቅ ሸፍነውት እንደነበረም ያስረዳሉ።

ወያኔ በአካባቢው የታጣቂ ኃይል ይንቀሳቀስበታል ስለዚህ እናንተም ከነሱ ጋር ልትወግኑ ትችላላችሁ በሚል ቀድሞ ታጥቆት የነበረውን የሕዝቡን መሣሪያ ሰብስቦ የወሰደ ሲሆን፣ አሁን እንደገና ይህንን የመሰለ ግፍ በሕዝቡ ላይ መፈፀሙ በአካባቢው ይንቀሳቀሳል በሚባለው ታጣቂ ድርጅት ላይ ሕዝቡ ጥላቻ እንዲያሳድር ሆን ተብሎ የተሰራ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ሕዝቡ ግን ድርጊቱን የፈፀመው ወያኔና የወያኔ ጃሌዎች ናቸው እያለ አፅንኦት ሰጥቶ እየገለፀ ይገኛል።

በተለይም ጥቃቱ የተፈፀመው ምንም አይነት የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና በሌላቸው ንፁህ አርሶ አደሮች ላይ መሆኑ ያሳዘናቸው የነቀምት ነዋሪዎች ተሰድደው ለመጡት ዜጎች የምግብና የመጠለያ እርዳታ ሲሰጡ የኦሮሚያ ፈጥኖ ደራሽ የተባለው ኃይል መልሶ እያባረራቸው መሆኑንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ከነቀምት ከተማ 47 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ሳሲጋ ወረዳ ሆርባታ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆኑት አንድ የጥቃቱ ሰለባ ሲገልፁ «ጥቃት ሊፈጽሙ የመጡት የለበሱት ሬንጀር ሙሉ ትጥቅ ያነገቡ ናቸው እናም አንዳንዶቹ ፊታቸውን በጨርቅ ጠቅልለዋል አሁን እንደሚባለው የጉሙዝ ብሔሮች ናቸው ጥቃቱን የፈፀሙት የሚለው ፍፁም ሐሰት ነው። እስከዛሬ ድረስ አብረን ነው የኖርነው እንዲህ ያለ ድርጊት ተፈፅሞ አይታወቅም ይሄ ታቅዶ በደንብ ተደራጅቶ የመጣ ኃይል ነው» ሲሉም እማኝነታቸውን ሰጥተዋል።

የወያኔው ቡድን ሕዝብን ከሕዝብ ማጋጨት ካለው ብርቱ ፍላጎት የመነጨና የተነሳ የፌዴራል ፖሊስ የሕዝብ ግንኙነት ነው የተባለ የወያኔ ሆድ አደር ተላላኪ በጉሙዝና በኦሮሞ ብሔሮች መካከል በተነሳ ግጭት 20 ሰው ሞቷል ነገሩም በርዶዋል በማለት መግለጫ የሰጠ ሲሆን መግለጫውን የተከታተሉ የወለጋ ነዋሪዎች እጅግ እንደተበሳጩና እንዳሳዘናቸው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ሆድ አደሩ የወያኔ ጃሌው አባዱላ ገመዳ ድርጊቱ ተፈጸመ ወደተባለው አካባቢ ሄደ የተባለ ቢሆንም ከነቀምት ከተማ ሳይወጣ ደርሶ የተመለሰ ቢሆንም ስለሁኔታው አንዲትም ትንፍሽ ሳይል መቅረቱ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ተብሎ በተዋቀረው የወያኔ ቡድን ተቀነባብሮ የተፀመ ተግባር በመሆኑ መግለጫ እንኳዋን እንዳይሰጥ መከለከሉን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ዘገባ ያስረዳል።

በጐንደር፣ በወለጋ፣ በጐጃም፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ውስጥ አንድ የተጠናከረ ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይል አለ ተብሎ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት በተዋቀረው የወያኔ ቡድን በኩል ከፍተኛ ስጋት ስላሳደረ የተለያዩ ምክንያቶች እየፈጠሩ እንዲህ ያለ አሰቃቂ ጭፍጨፋ በዜጐች ላይ አድርሰው መልሰው ከአሸባሪ ጋር የወገኑ ድርጅቶች የፈፀሙት ነው በማለት በፊልም ቀርፀው ለማሰራጨት ሆን ተብሎ የተሰራ መሆኑን የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሕዝቡ እነሱ ድርጊቱን መፈፀማቸውን ጠንቅቆ ማወቁንም ዘገባው አስረድቷዋል።

በተለይ ሰሞኑን በንፁሃን ዜጐች ላይ ይህንን የመሰለ ዘግናኝ እልቂት የፈፀመው የወያኔ ቡድን ያዘጋጀው ነው ያሉት የጥቃቱ ሰለባ ከሱዳን ድንበር ድረስ እየመጣ እርዳታ የምታደርጉለት ድርጅት አለ እያሉ የወያኔ ካድሬዎች ከዚህ ቀደም ብሎ ሕዝቡን የቁም ስቅሉን ሲያሳዩት እንደነበረ አውስተው አሁን በጠራራ ፀሐይ ይህንን የመሰለ ድርጊት መፈፀማቸው እንዳሳዘናቸው ገልፀዋል::

በተያያዘ ዜና ወያኔ ግንቦት 9ቀን2000 ዓ. ም. በወለጋ ህዝብ ላይ ጥቃት ካደረሰ በሁዋላ ጥቃቱን ያደረሰው ሌላ ሀይል ነው ለማሰኘት በአካባቢው መልሶ የፌዴራል ፖሊሶችን አስፍሮ የነበረ ቢሆንም ግንቦት 11ቀን 2000ዓ. ም. ከሌሊቱ 11 ሰዓት ላይ ለጊዜው ማን እንደሆነ ያልተወቀ የተቃዋሚ ታጣቂ ሀይል በሰፈረው ጦር ላይ ጥቃት ሰንዝሮ በርካታ ፖሊሶችን ለሞትና ለቁስለኝነት እንደዳረጋቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገለጸ::

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጥቃቱ የተሰነዘረባቸው የወያኔ ፌዴራል ፖሊሶች በድንጋጤ ለመሸሽ ሙከራ ሲያደርጉ ቁጥራቸው ለጊዜው ያልታወቀ በርካታ የሆኑት ሲቆስሉ ከ10 በላይ መገደላቸውን ገልጠዋል::
በዕለቱ አንድ ራሺያ ሰራሽ ኦራል መኪና በቆመበት የተቃጠለ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች ቀስለኞቹ ወደ ፖሊስ ሆስፒታል እና ጦር ሀይሎች ሆስፒታል እንደገቡም አስረድተዋል::

በቤንሻንጉል ክልል ውስጥም ተመሳሳይ ሁኔታዎች እየተከሰተ ሲሆን፣ በተለይ የወያኔ አቀንቃኝ ካድሬና የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ከአሶሳ እንዲለቁ ትዕዛዝ ተስጥቷቸው ወደ መሀል ሀገር ሸሽተው የነበረ ሲሆን በአካባቢው ሳይሸሹ የቀሩት የቤንሻንገል ክልል ባለስልጣናት ከተቃዋሚ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በጥያቄ ላይ መሆናቸውንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

በዚህም መሠረት ወያኔ እራሱ ንጹሀንን ዜጎች ፈጅቶ መልሶ ሌሎች ተቃዋሚ ናቸው በሚባሉ ግለሰቦች ላይ ሳይቀር ጣቱን እየቀሰረ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልጾ በቅርቡም ድርጊቱን የፈፀሙትን ይዣለሁ በማለት የራሱ ካድሬዎችን ጨምሮ በርካታ በድርጊቱ ላይ ያልተሳተፉ የተቃዋሚ አባላትን ለእይታ እንደሚያበቃ ይጠበቃል ሲልም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል::

በአሁን ሰዓት ወለጋ ውስጥ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ አዋሳኝ የመኪና ጉዞ የተገደበ ሲሆን፣ ጐንደርና ጋምቤላ አካባቢዎችም ቢሆን እንደወትሮው የመኪና እንቅስቃሴ እምብዛም የማይታይ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ ውስጥ የወያኔ ቡድን መቆጣጠር እየተሳነው መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች መኖራቸውን ከተለያዩ አካባቢዎች ከሚደርሱን ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል:: በወሎ መንገድ ሸዋሮቢት፣ በጐጃም አባይ በረሀ፣ በሐረር አዋሽ አካባቢ፣ በባሌ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና በሌሎችም አካባቢዎች እራሳቸውን ባደራጁ ግለሰቦችና ቡድኖች በዘረፋ ስራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ም ከደረሱን ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል::

በደቡብ ቤንሻንጉል ጉሙዝ አሶሳ ዞን በግዜንና በኩሙሩክ ወረዳዎች ድንበር ላይ 9 ሰዎች ተገደለው የያዙት ንብረትም እንደተወሰደባቸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተመሳሳይ በዚህ ወረዳ ውስጥ በአንድ አውቶቡስ ውስጥ ሲጓዙ የነበሩ 40 ተሳፋሪዎችም ዝርፊያ ከተካሄደባቸው በኋላ ግድያ እንደተፈፀመባቸው ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ወያኔ ለስልጣኔ እድሜ ማራዘሚያነት ያገለግሉኛል እያለ እና በችግር የተወጠረውን ለማስተንፈስ ይረዳኛል በሚል ሕዝቡን ከሕዝቡ እርስ በእርስ እያጋጨ በረሀብና በእንግልት እያሰቃየ ባለበት ወቅት እንደልባቸው ሲያሞላቅቃቸው የነበሩት ሹማምንት የነዳጅ አበል በመቀነሱ ብቻ ማኩረፋቸው ታወቀ፡፡
ለስልጣን ዕድሜው ማራዘሚያ እኛ መሆናችን እየታወቀ የአለም የነዳጅ ዋጋ ጨመረ፣ ኑሮ ተወደደ እየተባለ ከቀድሞው የነዳጅ አበል መቀነሱ ያበሳጫል በማለት የወያኔ ሹማምንቶች ቅሬታ በማሳደራቸው ለ3 ቀናት ወደ ስራ ገበታቸው ሳይገቡ መቅረታቸው ታውቋል፡፡

ከግንቦት 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የተደረገው የነዳጅ አበል ቅነሳ የወያኔ ሹማምንቶችን ያስኮረፈ ሲሆን፣ ከዚህ ቀደም ለመሸታ ቤት፣ ለሽንኩርት መግዣ ሲጠቀሙበት የነበረው ይኸው የነዳጅ ኮታ ወያኔ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ኪሣራ ውስጥ በመግባቱ ይህንን እርምጃ ሊወስድ የተገደደ መሆኑን የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮች፣ አሁንም በርካቶች እንዳኮረፉና የሕዝብን ገንዘብ ካላባከንን የሚል ወያኔያዊ አስተሳሰብ ውስጥ መኖራቸው ያሳዝናል ሲሉም ገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወያኔ ብቻውን ተወዳድሮ ያለምንም መራጭ እራሱ አሸናፊ በሆነበት በዚህ ምርጫና የስልጣን ክፍፍል ነባር ካድሬዎችና አዲሶቹ ካድሬዎች ግጭት መፍጠራቸው ታወቀ፡፡

ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ እንደገለፀው ከሆነ አዲሶቹ ምልምል የወያኔ ካድሬዎች ወደ ምርጫ እንዲገቡ እና ወያኔ ያለውን መጥፎ ገፅታ ለውጡልኝ ተብለው እንደተመለመሉ ገልፀው ከምርጫ በኋላ በምርጫ ያልተሳተፉትን ለቀበሌ መስተዳድር ያስቀመጧቸው ሲሆን ተመረጡ የተባሉትን ወጣቶች በሌላ ጊዜ ስልጣን ይሰጣችኋል በማለት እንዳሸሹዋቸው የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል፡፡

አንዴ አድኑኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሁለት እግሬ ቆሜያለሁ እያለ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ውስጥ ያለውና ግራ የተጋባው ወያኔ ሰሞኑን ገና የስልጣን ክፍፍል አድርገው ባላጠናቀቁበት ወቅት ይገባኛልና አይገባህም በሚል በነባርና በአዲስ ካድሬዎች መካከል ከፍተኛ ክፍተት በመፈጠሩ ለነህላዊ የራስ ምታት እንደሆነባቸው የምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት የአዲስ አበባ ሕዝብ መኖሪያ አጥቶ እየተሰቃየ ባለበት ወቅት እነዚህ ወጣትና አዲስ ካድሬዎችን ከስልጣን ባገለለ ማግስት የቀበሌ ቤት ባዶ የተለቀቀ ካለ መግባት ትችላላችሁ የሚል መመሪያ እንደተሰጣቸው የምንጮቹ ጥቆማ ገልፆ ቤት ለመስራት የጀመሩ በቀበሌ ቤት ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን ሳይቀር ለማስለቀቅ እየተጣደፉ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ ገልጿል፡፡